፳፪፣ ወለእመ መጽኡ አበዊሆን ወአኃዊሆን ይሳኑኑክሙ ንብሎሙ መሐርዎሙ እስመ ኢያውዕኡ አንስቲያሆሙ እምቀትል እስመ አኮ አንትሙ ዘወሀብክምዎሙ በእማንቱ፡ መዋዕል ኢትነስሑ ፣

አባቶቻቸውና ወንድሞቻቸውም ይጣሏችሁ ዘንድ ቢመጡ ሚስቶቻቸውን ወደ ጦርነት አላወጡምና ማሯቸው ፣ በዚያ ወራት ልጆቻችሁን እናንተ የሰጣችኋቸው አይደለምና አትጸጸቱ እንላቸዋለን አሏቸው ፡

፳፫፣ ወገብሩ ከማሁ ደቂቀ ብንያሚ ወነሥኡ አንስተ በኊላቌሆሙ እምእለ ይትዋነዩ ወተማሠጥዎን ወአተዉ ወገብኡ ውስተ ርስቶሙ፣

የብንያም ልጆችም እስራኤል እንደ ነገሯቸው አደረጉ ፣ ከሚጫወቱት ልጆች በቍጥራቸው መጠን ሴቶችን ነጥቀው ይዘው ወደርስታቸው ተመለሱ ፡

ወነደቁ ሎሙ አህጉረ ወነበሩ ውስቴቶን ፣

እኒህንም ሴቶች ይዘው ተመልሰው የጠፋውን አገር አቅንተው ኖሩ ፣ «ወለአህጉሪ ሆሙ፡ኒ አውዓይዎን በእሳት» ብሎ ነበርና እንዲህ አለ ፡

፳፬፣ ወአተዉ እምህየ ደቂቀ እስራኤል ብእሲ ብእሲ ውስተ ሕዝቡ ወውስተ ነገዱ ወአተዉ እምህየ ብእሲ ብእሲ ውስተ ርስቱ ፣

የእስራኤል ልጆችም አንዱም አንዱ ከሴሎ ተነሥተው ወደየወገናቸው ገቡ ፣ ነገደ ብንያምም አንዱም አንዱ ከሴሎ ተነሥተው ወደርስታቸው ገቡ ፡

፳፭፣ ወበእማንቱ፡ መዋዕል አልቦሙ ንጉሥ ለእስራኤል ብእሲ ብእሲ ዘአደሞ ቅድመ አዕይንቲሁ ይገብር፣

በዚያም ወራት ለእስራኤል ንጉሥ አልነበራቸውምና አንዱም አንዱም ሰው በፊቱ የወደደውን ያደርግ ነበር ፡ ሐተታ የማይገባ ሥራ መሥራታቸው የሚሠራ የሚቀጣ ንጉሥ ባይኖራቸው ነው ለማለት፣ ንጉሥ የሚነግሥበት ጊዜም ደርሷልና አልፎ አልፎ አነሣው ፡

ተፈጸመ አሪት ዘመሳፍንት የመሳፍንትን ነገር የሚናገር መጽሐፍ ደረሰ ተፈጸመ ፡፡

ለእግዚአብሔ ክብር ምስጋና ይግባው፤

ወስብሐት ለእግዚአብሔር



# አሪት ዘሩት

ዜና ዘሩት ሲል ነው ፣ የሩትን ነገር የሚናገር መጽሐፍ ይህ ነው ፣ ይህ አርእስት ነው፣ ፫፡ ፬ት ለመጻሕፍት አርእስት ሲሰጡ አርእስት ሰጥተውታል፣ እሷ ግን ነገሯን «ወኮነ በመዋዕለ ይኴንኑ መሳፍንት» ብላ ትጀምራለች ፡፡

## ምዕራፍ ፩

፩፣ ወኮነ በመዋዕለ ይኴንኑ መሳፍንት መጽአ ረኀብ ውስተ ብሔር፣

መሳፍንት በሚገዙበት ወራት እንዲህ ተደረገ ፣ በሀገሩ ረኀብ ሆነ ፣ ኮነ ያለውን መጽአ ረኀብ ብሎ ገለጠው ፤

ወሖረ ፩ ብእሲ እምቤተልሔም ዘይሁዳ ከመ ይንበር ውስተ ሐቅለ ሞዓብ ውእቱ፡ ወብእሲቱ፡ ወ፪ቱ፡ ደቂቁ ፣

አንድ ሰው ከሚስቱና ከሁለቱ ልጆቹ ጋራ በሞዓብ አውራጃ ይኖር ዘንድ የይሁዳ ክፍል ከምትሆን ከቤተልሔም ተነሥቶ ወደ ሞዓብ ሔደ ፤

፪፣ ወስሙ ለውእቱ፡ ብእሲ አቤሜሌክ ወስመ ብእሲቱ፡ ኑሐሚን ፣

የዚያ ሰው ስሙ አሜቤሌክ ነው፣ የሚስቱም ስም ኑሐሚን ይባላል ፣ ኑሐሚን ማለት ጥዕምት ፍሥሕት ብዝኀት ማለት ነው ፤

ወአስማተ ደቂቁ ፪ቱ፡ መሐሎን ወኬሊዎን ኤፍራታውያን እምቤተልሔም ዘይሁዳ ወሖሩ ውስተ ሐቅለ ሞዓብ ወነበሩ ህየ ፣

የሁለቱ፡ ልጆቹም ስማቸው የይሁዳ ዕጣ ከምትሆን ከቤተልሔም ወገን የሚሆኑ የኤፍራታ ሰዎች መሐሎንና ኬሊዎን ይባላል ፣ እነሱም ወደ ሞዓብ አውራጃ ሔደው በዚያ ተቀመጡ ፤

፫፣ ወሞተ አቤሜሌክ ምታ ለኑሐሚን ወተርፈት ይእቲ፡ ወደቂቃ ፪ኤሆሙ ፣

የኑሐሚን ባሏ አቤሜሌክ በሞዓብ ሞተ ፣ እርሷ ከሁለቱ፡ ልጆቿ ጋራ ብቻዋን ቀረች ፡

፬፣ ወነሥኡ ሎሙ አንስተ ሞዓብ ውያተ ስማ ለአሐቲ፡ ኡርፋ ወስማ ለካልዕታ ሩት ወነበሩ ህየ ወአከለ ፲ተ ዓመተ ፣

እነሱም ዘመድ እናብጅ ብለው ከሞዓባውያን ሴቶች ሚስት አገቡ ፣ /ሞዓባውያት ሴቶችን አገቡ/ ፣ የአንዲቱ ስሟ ዑርፋ የሁለተኛዪቱ ስሟ ሩት ይባላል ፣ በዚያም አሥር ዓመት ያህል ኖሩ ፤

www.ethiopianorthodox.org

፭፤ ወሞተ፡ ፪ኤሆሙ ውሉዳ ለኑሐሚን መሐሎን ወኬሌዎን ወተርፈት ይእቲ ብእሲት እምታ ወእም ፪ሆሙ ደቂቃ ፤

የኑሐሚን ሁለቱ ልጆቿ መሐሎንና ኬሌዎን ሞቱ ፤ የትም ሴት ከባሏና ከሁለቱ ልጆቿ ተለይታ ብቻዋን ቀረች ፤

፮፤ ወተንሥአት ይእቲ ወ፪ኤሆን መራዕዊሃ ወተመይጠት እምሐቅለ ሞዓብ እስመ ሰምዓት ከመ ተሠሃሎሙ እግዚአብሔር ለሕዝቡ ከመ የሀቦሙ እክለ ፤

እርሷ ከሁለቱ ምራቶቿ ጋር /ሁለቱን ምራቶቿን ይዛ/ ተነሣች ፤ እህል ይሰጣቸው ዘንድ እግዚአብሔር ወገኖቿ ፫ኤልን ይቅር እንዳላቸው ሰምታለችና ከሞዓብ አውራጃ ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሰች ፤ /ሐተታ/ ከኢየሩሳሌም የመጣ ሰው አግኝታ ጠየቀች ፤ እግዚአብሔር አገራችንን ታርቋታል ማለት ዝናም ለዘር ፤ ጠል ለመከር ሰጥቷታል አላት፤ ይህንም ሰምታ ከዚህ ደስ ብሎኝ እኖራለሁ እንዳልል ባሌም ልጆቼም አልቀዋል ፤ ሀገሬ ልግባ ብላ ተነሥታለች ፤

፯፤ ወወፅአት እምውእቱ መካን ኀበ ይነብራ ፪ኤሆን መራዕዊሃ ምስሌሃ ወሖራ ውስተ ፍኖት ከመ ይእትዋ ውስተ ምድረ ይሁዳ ፤

ሁለቱ ምራቶቿ ከርሷ ጋራ ከሚኖሩበት ቦታ ወጥታ ወደ ይሁዳ ሰባ ይሔዱ ዘንድ መንገዳቸውን ሔዱ ፤

፰፤ ወትቤሎን ኑሐሚን ለመራዕዊሃ ሑራ እትዋ አብያተ አበዊክን ወእማቲክን ወይግበር እግዚአብሔር ምሕረቶ ምስሌክን ከመ ገበርክን ምሕረተ ምስለ እለ ሞቱ ወምስሌየ ፤

ኑሐሚንም ምራቶቿን ወልዳ ትተካልናለች አትሉኝ አፍጅቻለሁ ፤ ትወልድልናለች አትሉኝ አርጅቻለሁ ወደ እናት አባታችሁ አገር ተመለሱ ለሞቱት ባሎቻችሁና ለእኔ በጎ ነገርን እንዳደረጋችሁ እግዚአብሔር ይቅርታውን ያድርግላችሁ አለቻቸው ፤ ለኑሐሚን ማድረግ ለሞቱት ማድረግ ነውና /ወረታ መክፈል ነውና/ ፤

፱፤ ወየሀብክን እግዚአብሔር ትርከባ ምሕረተ ወዕረፍተ ውስተ አብያተ አምታቲክን ወሰዓመቶን ፤



በባሎቻችሁ ቤት ዕረፍትን ታገኙ ዘንድ እግዚአብሔር ቸርነቱን ይስጣችሁ ብላ ሳመቻቸው ፤

፲፤ ወጸርሐ ወበከያ ወይቤላሃ ምስሌኪ ንገብእ ውስተ ሕዝብኪ ፤

እነርሱም ከአንቺ ጋር ወደ ወገኖችስ እንመለሳለን /እንሔዳለን/ ብለው ድምፃቸውን ከፍ ከፍ አድርገው አለቀሱ ፤

፲፩፤ ወትቤሎን ኑሐሚን እትዋ አዋልድየ ለምንት ትመጽኣ ምስሌየ ቦኑ ዘብየ ዓዲ ውሉድ ውስተ ከርሥየ እለ ያወስቡክን ፤

ኑሐሚንም ልጆቼ ከእኔ ጋራ ለምን ትሔዳላችሁ? ወደ ሀገራችሁ ተመለሱ እንጂ፤ ዳግመኛ ተወልደው አድገው ያገቧችሁ ዘንድ በሆዴ ልጆች አሉኝን አለቻቸው ፤

፲፪፤ እትዋ እንከሰ አዋልድየ እስመ ረሳእኩ እምአውስቦ ዘእም ወለድኩ ውሉደ ወትጸንሐሆሙኑ እስከ አመ ይልሕቁ ፤

ልጆቼ እንግዲህስ ወደ ሀገራችሁ ተመለሱ ባል ከማግባት አርጅቻለሁና ልጅ ለመውለድ ተስፋ አለኝ ብዬ ባል ባገባም የምወልዳቸው ልጆች እስኪያድጉ ድረስ ትጠብቋቸዋላችሁን ፤

፲፫፤ ወታጸንዓ ርእሰክን ወኢትትዋሰባ አልቦ አዋልድየ እስመ መረረ ተኒ ነፍስየ ጥቀ ፈድፋደ እምኔክን ወፅአት እምኔየ እደ እግዚአብሔር ፤

ይህስ ባይሆን ልጆቼን አግብታችሁ ራሳችሁን ባጸናችሁ ነበር ፤ እንጂ ሌላ ባላገባች ሁም ነበር ፤ ነገር ግን ከእናንተ መለየት የተነሣ ሰውነቴ ፈጽማ አዝናለችና ፤ የእግዚአብሔር ረድኤትም ከእኔ ተለይ ታለችና ልጆቼ እንዲህ አይደለም ተመለሱ አለቻቸው ፤

፲፬፤ ወጸርሐ ካዕበ ወበከያ ወሰዓመታ ለዐርፍ ሐማታ ወተመይጠት ኀበ ሕዝባ ወሩትሰ ተለወታ፤

ዳግመኛ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው አለቀሱ ፤ አማቷ ኑሐሚን ኡርፍን ሳመቻት ፤ አንድም «ወሰዓመታ ዐርፍ ለሐማታ ይላል» ፤ ዐርፍ ከሞተ አቴቴ ምን አለኝ ከአማቴ የምትል ናትና የአማቷን ጉልበት ስማ ወደ ወገኖቿ ተመለሰች ፤ ሩት ግን ከሞተ አቴቴ ምን አለኝ ከአማቴ የማትል ደግ ሴት ናትና ተከተለቻት ፤

፲፭፤ ወትቤላ ኑሐሚን ለሩት ናሁ አተወት ካልዕትኪ ኀበ ሕዝባ ወኀበ አማልክቲሃ እትዊ አንቲኒ ምስለ ካልዕትኪ፤

www.ethiopianorthodox.org

ኑሐሚንም ሩትን እነሆ ባልን ጀራሽ ዑርፍ ወደ ወገኖቿና ወደ ጣዖቶቿ ተመለሰች ፤ አንቺም ከባልንጀራሽ ጋር ተመለሽ አለቻት ፡፡

፲፮፤ ወትቤላ ሩት ኢይትከሃለኒ ከመ እኅድጊ ወከመ እትመየጥ እምድኅሬኪ ኀበ ሖርኪ አንቲ አሐውር ውኀበ ኀደርኪ አኀድር ሕዝብኪ ሕዝብየ ወአምላክኪ አምላኪየ ውኀበ ሞትኪ እመውት ወህየ እትቀበር ፤

ሩትም እተውሽ ዘንድ አንችንም ትቼ እመለስ ዘንድ አይቻለኝም፤ አንቺ ከሔድሽበት እሔዳለሁ ፤ ከአደርሽበትም አድራለሁ ወገንሽ ወገኔ ፈጣሪሽ ፈጣሪዬ ነውና በሞትሽበት እሞታለሁ በተቀበርሽበትም እቀበራለሁ ፡፡

፲፯፤ ከመዝ ለይረስየኒ እግዚአብሔር ወከመዝ ለይኩን ከመ አልቦ ዘይፈልጠኒ እምኔኪ ዘእንበለ ሞት፤

ከሞት በቀር ከአንቺ የሚለየኝ እንደሌለ ብላ የያዘችውን እየጣለች እንዲህ ይጣለኝ እግዚአብሔር የአንቺን ሞት ለእኔ ያድርገው አለቻት ፡፡

፲፰፤ ወሶበ ርእየት ኑሐሚን ከመ አጽንዓት ልባ ለሐዊር ምስሌሃ ኅደገት እንከ ብሂሎታ ፤

ኑሐሚንም ሩት ከእርሷ ጋራ ለመሔድ ልቡናዋን እንደ አጸናች ባየች ጊዜ ከዚያ በኋላ ተመለሽ ማለቷን ተወች ፡፡

፲፱፤ ወሖራ ፪ኤሆን እስከ በጽሓ ቤተልሔም ወደምፀት ኵላ ሀገር በእንቲአሃ ወይቤልዋ ሕያውትኑ አንቲ ኑሐሚን ፤

ኑሐሚንና ሩትም ቤተልሔም እስኪደርሱ ድረስ በአንድነት ሔዱ ፤ መምጣቷም በሀገር ሁሉ ተሰምቶ ሕዝቡ ይወዷት ነበርና ኑሐሚን ደኅና ነሽ ? እያሉ በእልልታ ተቀበሏት ፡፡

፳፤ ወትቤሎን ኢትስምያኒ ኑሐሚን አላ ስምያኒ መራረ እስመ መረርኩ ፈድፋደ ወብዙኃ ፤

ኑሐሚንም ፈጽሜ አዝኛለሁና ምርርት በሉኝ እንጂ ለምን ጥዕምት ትሉኛላችሁ? ኀዝንት በሉኝ እንጂ ለምን ፍሥሕት ትሉኛላችሁ ? ሕጽጽት በሉኝ እንጂ ለምን ምልዕት ትሉኛላችሁ ? አለቻቸው ፡፡

፳፩፤ ወአንሰ ምልዕትየ ሖርኩ ወእራቅየ አግብአኒ እግዚአብሔር ለምንት ትብላኒ ኑሐሚን እንዘ እግዚአብሔር አሕሰረኒ ወፈድፋደ አሕመመኒ ፤

እኔ ብዙ ሁኜ ሔድኹ ፤ እግዚአብሔር ብቻዬን መለሰኝ፤ ስለ



ዚህ እግዚአብሔር አዋርዶኝ ሳለ ፤ ፈጽሞም አሳዝኖኝ ሳለ ለምን ፍሥሕት ትሉኛላችሁ?

፳፪፤ ወገብአት ኑሐሚን ወሩት መርዓታ ሞአባዊት ወአተዋ እምሐቅለ ሞዓብ ወበጽሓ ውስተ ቤተልሔም አመ ቀዳሚ ማዕረረ ሰገም ፤

ኑሐሚንም የሞዓብ ሰው ከምትሆን ከምራቷ ከሩት ጋር ከሞዓብ አውራጃ ተመልሳ በገብሱ መከር መጀመሪያ ወደ ቤተልሔም ደርሰው ከዚያ ገቡ ፡፡

## ምዕራፍ ፪

፩፤ ወባቲ ለኑሐሚን ብእሲ ዘየአምሮ ለምታ ወውእቱሰ ብእሲ ጽኑዕ ወከሃሊ እምአዝማዲሁ ውእቱ ለአቤሜሌክ ወስሙ ባዖስ፤

ለኑሐሚን ባሏን የሚያውቀው /በመውረስ የሚዘመደው/ ሰው ነበራት ፤ ያም ሰው በእውቀት የጸና ከአቤሜሌክ ከዘመዶቹ ወገን የሚሆን የሚቻለው ነበር ፤ ስሙም ባዖስ ይባላል ፤ /ሐተታ/ ጽኑዕ የዕውቀት የነገር ፤ ከሃሊ የብዕል ነው ፡፡

፪፤ ወትቤላ ሩት ሞዓባዊት ለኑሐሚን እሑርኑ ውስተ ገራህት እዕሪ እክለ ኀበ እለ ረከብኩ ሞገሰ ወትቤላ ሑሪ ወለትየ ፤

የሞዓብ ሴት የምትሆን ሩት ኑሐሚንን ባለሟልነትን ከአገኘሁበት ቦታ እህልን ለቅሜ እመጣ ዘንድ ወደ ቃርሚያ ልሒድን አለቻት ፤ እሷም ልጄ ሒጂ እግዚአብሔር ይከተልሽ አለቻት ፡፡

፫፤ ወሖረት ወአረየት እምውስተ ገራህት እንዘ ትትልዎሙ ለእለ የዓጽዱ ወበጽሐት ውስተ ፩ዱ ኀብር እምገራህቱ ለባዖስ ዘእም ዘመዱ ለአቤሜሌክ ፤

አጫጆችን እየተከተለች ከእርሻው ልትለቅም ሔደች የአቤሜሌክ ወገን ከሚሆን ከባዖስ እርሻ ወደ አንድ ወገን ደረሰች፡፡

፬፤ ወመጽአ ባዖስ እምነ ቤተልሔም ወይቤሎሙ ለእለ የዓጽዱ እክለ እግዚአብሔር ምስሌክሙ ወይቤልዎ ይባርከ እግዚአብሔር፤

ባዖስም ከቤተልሔም መጥቶ እህል የሚያጭዱ ሠራተኞቹን እግዚአብሔር ከእናንተ ጋር ይሁን ማለት እግዚአብሔር ኃይል ይስጣችሁ አላቸው፤ እነርሱም እግዚአብሔር ያክብርህ ያብዛህ አሉት፡፡

www.ethiopianorthodox.org

፭፣ ወይቤሎ ባዖስ ለወልዱ ዘይቀውም ኅዕለ እለ የዓጽዱ እንተ መኑ ዛቲ ወለት ፤

ባዖስም በአጫጆቹ ላይ የተሾመ ብላቴናውን ይህች ብላቴና የማን ልጅ ናት ? አለው ፤ በምን አውቆ ቢሉ በእንግድነቷ ስታፍር አይቶ ፤ አንድም በግብሯ በ፳ኤል አጫጅ ለማራሪ ፤ ማራሪ ለወፍ እንዲያተርፍ ሥርዓት ተሠርቷል ፤ እርሷ ግን አጥርታ ስትለቅም አይቶ ፤

፮፣ ወአውሥአ ውእቱ ወልድ ዘይቀውም ኅዕለ እለ የዓጽዱ ወይቤሎ እንታክቲ ወለት ሞዓባዊት እንተ ገብአት ምስለ ኑሐሚን እምሐቅለ ሞዓብ ፤

በአጫጆቹ ላይ የተሾመው ብላቴናም ይህችማ ከኑሐሚን ጋራ ከሞዓብ አውራጃ የመጣች የሞዓብ ሴት ናት ብሎ መለሰለት ፤

፯፣ ወትቤሎ እዕሪ ወአስተጋብእ እምዘወድቀ እምከላስስት እምድኅሬሆሙ ለእለ የዓጽዱ ወመጽአት ወቆመት እምነግህ እስከ ይእዜ ወኢኀደገት ንስቲተ እምውስተ ገራህት ፤

እርሷም ከአጫጆች በኋላ ከነዶው የወደቀውን እንድ ለቅም ብላ መጥታ ከጧት እስከአሁን ቃርሚያ ስትለቅም የቆየች ናት አጥርታ ከመልቀሟ የተነሣም ጥቂትስ እንኳ ከቃርሚያው አልተወችም ፤ አንድም ከአለማግኘቷ የተነሣ አንድ ዛላስ እንኳ በእቃዋ አላኖረችም ፤

፰፣ ወይቤላ ባዖስ ለሩት ኢሰማዕኪኑ ወለትየ ኢትባኢ ውስተ ገራህተ ባዕድ ለአስተጋብአ ወኢትሑሪ እምዝየ ትልዊዮን ለአዋልድየ፤

ባዖስም ሩትን አንቺን መውረስ እንዲገባኝ አልሰማሽምን ልጄ ቃርሚያ ለመልቀም ወደ ባዕድ እርሻ አትግቢ ፤ ከዚህም አትሂጂ ልጆቼን በየት ዋሉ ፤ በየት አደሩ እያልሽ ተከተያቸው ፤ አንድም /ኢሰማዕኪኑ ወለትየ/ ፤ ልጄ ወደ ባዕድ ርሻ ለመልቀም አትግቢ የተባለውን የህገሩን ልማድ አልሰማሽምን ? ከዚህ ወደ ሌላ አትሒጅ ልጆቼን ተከተያቸው እንጂ አላት ፤

፱፣ ወነጽሪ ውስተ ገራህት ኀበ የዓጽዱ ወትልዊዮሙ ናሁ አዘዝኩ ደቀ ከመ አልቦ ዘይለክፈኪ ወእመኒ ጸማእኪ ሑሪ ኀበ ንዋይ ወስትዪ እምዘአምጽኡ ደቅ ፤

አጫጆቹ የሚያጭዱበትን ቦታ ተመልከች ፤ የሚከለክልሽም እንዳይኖር እነሆ ልጆቼን አዝዤልሻለሁ ውሃ ብትጠ



ሚም ወደ ጓዝ ሔደሽ የእኔ ብላቴኖች ከአመጡት ውሃ ጠጪ አላት ፤

፲፣ ወወድቀት በገጸ ወሰገደት ውስተ ምድር ወትቤሎ እመረከብኩ ሞገሰ በቅድመ አዕይንቲከ ዑቀኒ እስመ እንግዳ አነ ፤

እግር ከግንባር አድርጋ ሰግዳ በፊትህ ባለሟልነትን ከአገኘሁስ እኔ እንግዳ ነኝና እወቀኝ አለችው ፤

፲፩፣ ወአውሥአ ባዖስ ወይቤላ ዜና ዜነዉኒ ኵሎ ዘገበርኪ ምስለ ሐማትኪ እምድኅረ ሞተ ምትኪ ወእፎ ኀደጊ አባኪ ወእመኪ ወብሔረ ሙላድኪ ወመጻእኪ ኀበ ሕዝብ ዘኢተአምሪ ትካት ፤

ባዖስም ባልሽ ከሞተ በኋላ ለአማትሽ ያደረግሽውን በጎ ነገር ሁሉ ነግረውኛል ፤ አባት እናትሽንና የተወለድሽበትን ሀገር ትተሽ ቀድሞ ወደማታውቂው ወገን እንደ ምን እንደ መጣሽ ነግረውኛል፤

፲፪፣ ወይዕሢኪ እግዚአብሔር በከመ ገበርኪ ወይኩን ዕሤትኪ ፍጹመ በኀበ እግዚአብሔር አምላከ ፳ኤል ዘመጻእኪ ኀቤሁ ከመ ትትአመኒ በክነፊሁ ፤

ለአማትሽ በጎ ነገርን እንደ አደረግሽ እግዚአብሔር ዋጋሽን ይስጥሽ በክንፈ ረድኤቱ ታምኚ ዘንድ ወደ እርሱ በመጣሽበት በእስራኤል ፈጣሪ በእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋሽ ፍፁም ይሁን ብሎ መለሰላት ፤

፲፫፣ ወትቤሎ ሩት ረከብኩ ሞገሰ በቅድመ አዕይንቲከ እስመ አስተፍሣሕከኒ ወናዘዝካሁ ለልበ አመትከ ወናሁ አነ እከውነከ ከመ አሐቲ እምነ አዕማቲከ ፤

ሩትም ደስ አሰኘተኸኛልና የእኔን የባሪያህን ልቡና ፤ አረጋግተኸዋልና በፊትህ ባለሟልነትን አገኘሁ ፤ እነሆ እኔም ከባሪያዎችህ እንደ አንዲቱ እሆንልሃለሁ አለችው፤

፲፬፣ ወይቤላ ባዖስ ሶበ ኮነ ጊዜ ምሳሕ ንዒ ዝየ ወብልዒ ኅብስተ ወትጸብሒ ኅብስተኪ በብሒዕ ወነበረት ሩት እመንገለ ገቦሆሙ ለእለ የዓጽዱ ወአስተጋብአ ላቲ ባዖስ ጥሕነ ወበልዐት ወፀግበት ወአትረፈት ፤

ባዖስም በምሳ ጊዜ ወደዚህ መጥተሽ እንጀራ ብዪ ፤ እንጀራሽንም በመጣጣው /በወጥ/ አጥቅሺ አላት ፤ ሩትም በአጫጆቹ አጠገብ ተቀመጠች ፤ ባዖስም በሶውን ታፍኖ ሰጣት ፤ በልታ ጠግባ አተረፈች ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፭፣ ወተንሥአት ትትቀረም ወአዘዞሙ ባዖስ ለደቁ ወይቤሎሙ ለትዕሪ ማዕከለ ከላስስት ወኢታስተሐፍርዋ ፣

ትለቅም ዘንድ ተነሣች ባዖስም ብላቴኖቹን በነዶው መካከል ገብታ ትልቀም አትከልክሏት ፤

፲፮፣ ወፁሩ ላቲ እምዘ አስተጋብአት ወኅድጉ ላቲ ወትብላዕ ወትዕሪሂ ወኢትገሥጽዋ ፣

የሰበሰበችውንም ተሸከሙላት /አሸክሟት/ ፣ ተዉላት አትቅረጧት ለቅማ ትብላ አትቆጧት ብሎ አዘዛቸው ፤

፲፯፣ ወዐረየት እምገራህት እስከ መስየ ወዘበጠቶ ለዝክቱ ዘአስተጋብአት ወኮነ ሰገም በመስፈርተ ኢፍ ፣

እስኪመሽም ድረስ ከእርሻው ለቀመች ፣ የሰበሰበችውንም ወቃችው፣ የወቃችውም ገብስ ኢፍ በሚባል መስፈሪያ ሆነ ማለት አሥር ላዳን ሆነ ኢፍ አሥር ላዳን የሚይዝ ነውና ፤

፲፰፣ ወነሥአት ወአተወት ሀገረ ወርእየት ሐማታ ዘዐረየት ወአምጽአት ሩት ወወሀበታ ዘአትረፈት እምድኅረ ጸግበት ፣

ይህንም ይዛ ወደከተማ ገባች ፣ አማቷ ኑሐሚንም የለቀመችውን አየች ፣ ሩትም በልታ ከጠገበች በኋላ ያተረፈችውን አውጥታ ሰጠቻት ፤

፲፱፣ ወትቤላ ሐማታ በአይቴ ዐረይኪ ዮም ወበአይቴ ገበርኪ ቡሩከ ለይኩን ዘአእመረኪ ፣

አማቷ ኑሐሚንም ዛሬ ወዴት ለቀምሽ ? ወዴትስ ስትሠሪ ዋልሽ ? በፍቅር ያወቀሽ ሰው ፣ አንድም ያደረግሽውን በጐነት አውቆ ይህን ያደረገልሽ ሰው የተመሰገነ ይሁን አለቻት ፤

ወአይድዓታ ሩት ለሐማታ በአይቴ ገብረት ወነገረታ ስሞ ለውእቱ ብእሲ ዘነቤሁ ወዓልኩ ዮም ባዖስ ውእቱ ፣

ሩትም ለአማቷ በወዴት ስትሠራ እንደዋለች ነገረቻት፣ ዛሬ የዋልኩበት የዚያም ሰው ስሙ ባዖስ ይባላል ብላ ነገረቻት ፤

፳፣ ወትቤላ ኑሐሚን ለመርዓታ ቡሩክ ውእቱ እግዚአብሔር እስመ ኢኀደገ ምሕረቶ ምስለ ሕያዋን ወምስለ ምውታን ፣

ኑሐሚንም ምራቷን ሕያዋን ከምንሆን ከእኛ ጋርና ሙታን ከሆኑ ከእነ አቤሜሌክ ጋር ቸርነቱን አልተወምና እግዚአብሔር ክቡር ምስጉን ነው አለቻት ፤



ወትቤላ ኑሐሚን ብእሲሁሰ ቅሩብነ ውእቱ እምእለ ይትሐመዉነ፣

ኑሐሚንም ሰውየውስ እኛን መውረስ ከሚገባቸው ወገን አቅራቢያችን ነው አለቻት ፤

፳፩፣ ወትቤላ ሩት ለሐማታ እስመ ይቤለኒ ምስለ አዋልድየ ትልዊ እስከ የኀልቅ ማዕረርነ ፣

ሩትም አማቷ ኑሐሚንን አዝመራችን እስኪያልቅ ድረስ ልጆቼን ተከተይ ብሎኛልና እከተላለሁ አለቻት ፤

፳፪፣ ወትቤላ ኑሐሚን ለሩት መርዓታ ሠናይ ወለትየ ሶበ ትተልዊ አዋልዲሁ ወኢይርከቡኪ ውስተ ገራህተ ባዕድ፣

ኑሐሚንም ምራቷ ሩትን ልጄ ልጆቹን ብትከተይ መልካም ነው፣ ከባዕድ ሰው /ከሌላ ሰው/ እርሻም አያግኙሽ አለቻት፣

፳፫፣ ወተለወቶን ሩት ለአዋልደ ባዖስ ከመ ትዕሪ እስከ አመ የኀልቅ ማዕረረ ሰገም ወሥርናይ ወነበረት ምስለ ሐማታ፣

ሩትም የገብሱና የስንዴው መከር /አዝመራ/ እስኪያልቅ ድረስ የባዖስን ልጆች ተከተለቻቸው ፣ ከአማቷ ከኑሐሚን ጋራም ኖረች ፡፡

## ምዕራፍ ፫

፩፣ ወትቤላ ኑሐሚን ለሩት መርዓታ ወለትየ ኢየኃሥሥኑ ለኪ ዕረፍተ ከመ ትሠኒ ላዕሌኪ፣

ኑሐሚን ምራቷ ሩትን ልጄ አንቺ ለእኔ በጎ ነገር ስታደርጊልኝ እኔስ ላንቺ በጎ ነገርን አላደርግምን አለቻት ፤

፪፣ ወይእዜኒ አኮኑ ባዖስ ማእምርነ ዘምስለ አዋልዲሁ ሀሎኪ ናሁ ውእቱ ይገብር ውስተ ዓውደ እክሉ ዮም በዛቲ ሌሊት ፣

አሁንም ከልጆቹ ጋር ያለሽ በት ባዖስ በመውረስ የሚያው ቀን አይደለምን ? እነሆ ዛሬ አውድማውን ይጥላል ፣ በዚችም ሌሊት ከአውድማው ያድራል፣

፫፣ ወአንቲሰ ተሐፀቢ ወተቀብዒ ወተላበሲ አልባሲኪ ወሑሪ ኀበ ዓውደ እክሉ ወአልቦ ሰብእ ዘይሬእየኪ እሰከ የኀልቅ በሊዐ ወሰትይ፣

አንቺ ግን ገላሽን ታጥበሽ ፣ ሽቱ ተቀብተሽ ፣ ልብስሽን ለብሰሽ ወደ እህሉ አውድማ ሒጅ ፤ አንድም ሒደሽ ከክምሩ በኋላ ዘወር ብለሽ ተቀመጭ ፣ መብሉ መጠጡ እስኪፈጸም ድረስ የሚያይሽ ሰው አይኑር አለቻት ፣ ፳ኤል ዓይን አፋር ናቸውና ፣ ሲበሉ ሲጠጡ የሚያያቸው አይወዱ ምና እንዲህ አለች ፤

www.ethiopianorthodox.org

፬፣ ወሶበ ሰከበ አእምሪ መካኖ ኀበ ኖመ ወህየ ሑሪ ወክሥቲ ነበ እገሪሁ ወስክቢ ወውእቱ ለሊሁ ይኤዝዘኪ ዘከመ ትገብሪ ፣

በተኛ ጊዜም የተኛበትን ቦታ አውቀሽ ከዚያ ሒደሽ ከእግሩ ዘንድ ገለጥ አድርገሽ ተኚ ፣ ከቀኝ ወደ ግራ ከግራ ወደ ቀኝ ሲዘዋወር ያገኝሻል ፣ እኔ ገረድህ ሩት ነኝ ፣ አወራረስ አቈራረስ ይገባሃል /ይገባኛል/ ብዬ መጥቻለሁ በይው፣ ያን ጊዜ እንደምታደርጊው እሱ ያዝሻል አለቻት ፤

፭፣ ወትቤላ ሩት ኵሎ ዘከመ ትቤልኒ እገብር ፣

ሩትም ያልሽኝን ሁሉ አደርጋለሁ አለቻት ፤

፮፣ ወሖረት ኀበ ዓውደ እክል ወገብረት ኵሎ ዘከመ አዘዘታ ሐማታ ፣

ወደ እህሉ አውድማ ሒዳም አማቷ ኑሐሚን እንደ አዘዘቻት አደረገች ፤

፯፣ ወበልዐ ወሰትየ ባዖስ ወተፈሥሐ ልቡ ወሖረ ወሰከበ ኀበ ክምር ወመጽአት ጽሚተ ወከሠተት ኀበ እገሪሁ ወሰከበት ፣

ባዖስም በልቶ ጠጥቶ ልቡና ውን ደስ ብሎት ከክምሩ ዘንድ /ከምርቱ/ አጠገብ ተኛ፣ እሷም ቀስ ብላ መጥታ ከእግሩ ዘንድ ገልጣ ተኛች ፤

፰፣ ወመንፈቀ ሌሊት ከዊኖ ነቅሐ ባዖስ ወደንገፀ ወረከበ ብእሲተ ኀበ እገሪሁ ፣

መንፈቀ ሌሊት በሆነ ጊዜ ባዖስ ከእንቅልፉ ነቃ ፣ ከእግሩ አጠገብ ሴት ተኝታ አግኝቶ ደነገጠ ፤

፱፣ ወይቤላ መኑ አንቲ ወትቤሎ አነ ሩት አመትከ ወክድነኒ ጽንፈ ልብስከ እስመ መስተሐምው አንተ ፣

አንቺ ማነሽ ? አላት ፣ እርሷም እኔ ባሪያህ ሩት ነኝ ፣ አንተ እኔን መውረስ የሚገባህ ነህና የልብስህን ጫፍ አልብሰኝ አለችው ፤

፲፣ ወይቤላ ባዖስ ቡርክት አንቲ ለእግዚአብሔር ወለትየ እስመ ሐየስት ምሕረት ደኀሪት እምቀዳሚትኪ ዘኢሖርኪ ወኢተለውኪ ወራዙተነ ነዳያነ ወአብዕልተ ፣

ባዖስም ልጄ አንቺ ለእግዚአብሔር የተባረክሽ ፍጥረት ነሽ ፣ ሽማግሌ ነው ብለሽ ወደ ጐልማሳ ፣ መልከ ጥፉ ነው ብለሽ ወደመልከ መልካም ፣ ድኃ ነው ብለሽ ወደ ባለጠጋ ያልሔድሽ /አለመሔድሽ/ ከቀድሞው በጐነትሽ የዛሬው በልጧልና ፤



፲፩፣ ወይእዜኒ ወለትየ ኢትፍርሒ ኵሎ ዘትቤልኒ እገብር ለኪ ወየአምር ኵሉ ነገደ ሕዝብየ ከመ ብእሲተ ኃይሉ አንቲ ወከመ መስተሐምው አነ ወባሕቱ ቦ መስተሐምው ዘይቀርብ እምኔየ፣

አሁንም ልጄ አትፍሪ ፣ ያልሽኝን ሁሉ አደርግልሻለሁ ፣ አንቺ የሠራዊታቸው አለቃ ሚስት እንደሆንሽ እኔም አወራረስ አቆራረስ የሚገባኝ እንደ ሆንሁ ወገኖቼ ሁሉ ያውቃሉ፣ ነገር ግን በአወራረስ በአቈራረስ ከእኔ የሚቀርብ አለ ፤

፲፫፣ ቢቲ ዛተ ሌሊተ ወሶበ ጸብሐ ለእመ ተሐመወ ሠናይ ውእቱ ለይትሐመውኪ ወለእመሰ ኢፈቀደ ይትሐመው ውእቱ ሕያው እግዚአብሔር ከመ አነ እትሐመውኪ ሠቢቲ እስከ ይጸብሕ ፣

የዛሬን ሌሊት እደሪ ፣ ከነጋ በኋላ ያ ሰውዬ እወርሳለሁ ቢል በጎ ነው ፣ ባይወድ ግን እሱን ጠይቄ እኔ እንድወርስሽ እግዚአብሔር ሕያው ነው ፣ እስኪነጋ ድረስ እደሪ አላት ፤

፲፬፣ ወቤተት ኀበ እገሪሁ እስከ ይጸብሕ ወተንሥአት እንበለ ይትረአይ ሰብእ ፣

እስኪነጋም ድረስ ከእግሩ በታች ተኝታ አደረች ፣ ሰውና ሰው ሳይተያይ ጨለማ ጭምር ሳለ ተነሣች ፤

፲፭፣ ወይቤ ባዖስ አልቦ ዘየአምር ከመ መጽአት ብእሲት ኀበ ዓውደ እክል ፣

ባዖስም ወደ እህሉ አውድማ ሴት እንደመጣች የሚያውቅ ሰው አይኑር አለ ፤

፲፮፣ ወይቤላ አምጽኢ ልብሰ ዘላዕሌኪ ወአኀዘ ወሰፈረ ውስቴቱ ሳድሰ እክለ ሰገም ወአፆራ ወቦአት ውስተ ሀገር ፣

የለበስሽውን ልብስ አምጭ ብሎ ልብሷን ዘርግቶ እንዳታፍር ስድስት ላዳን ገብስ ሰፍሮ በልብሷ ቋጥሮ አሸከማት ፣ ይዛ ወደ ሀገር ገባች ፤

፲፯፣ ወአተወት ሩት ኀበ ሐማታ ወትቤላ ምንት ዝንቱ ወለትየ ወአይድአታ ኵሎ ዘከመ ገብረ ላቲ ውእቱ ብእሲ ፣

ሩትም ወደ አማቷ ወደ ኑሐሚን ገባች ፣ እሷም ልጄ ይህ ምንድን ነው ? አለቻት ፣ እሷም ያ ሰው ያደረገላትን ሁሉ ነገረቻት ፤

፲፰፣ ወትቤላ እሉንተ ስድሰ እክለ ሰገም ወሀበኒ ወይቤለኒ ኢትእትዊ እራቀኪ ኀበ ሐማትኪ ፣

ወደ አማትሽ እራቁትሽን /ባዶሽን/ እንዳትመለሽ ብሎ ይህን ስድስት ላዳን ገብስ ሰጠኝ አለቻት ፤

www.ethiopianorthodox.org

፲፰፣ ወትቤላ ንበሪ ወለትየ እስከ ትሬእዪ ከመ ኢይወድቅ ቃልየ እስመ ኢያረምም ውእቱ ብእሲ ወኢየዓርፍ ዮም እስከ ይገብሮ ለዝንቱ ነገር ፣

ያ ሰው ዝም አይልምና ይህንም ነገር እስኪያደርገው ድረስ አያርፍም እና ከቃሌ የሚዘነጋ /የሚቀር/ እንደሌለ እስክታዪ ድረስ ልጄ አርፈሽ ተቀመጪ አለቻት ።

## ምዕራፍ ፬

፩፣ ወዐርገ ባዖስ ኀበ አንቀጽ ወነበረ ህየ ወመጽአ ዝኩ፡ መስተሐምው ዘይቤ ባዖስ ይኀልፍ ወይቤሎ ባዖስ ገሐስ ወንበር ዝየ እስከ ንትናገር ወግኀሠ ወነበረ ፣

ባዖስ ወደ አደባባይ ወጥቶ በዚያ ተቀመጠ ፣ ባዖስ ከእኔ የሚቀርብ አወራረስ አቆራረስ የሚገባው አለ ያለው ሰው አልፎ ይሔድ ዘንድ ወደ አደባባይ መጣ ፣ ባዖስም እስክ ንነጋገር ድረስ ወደ አደባባይ ገብተህ ተቀመጥ አለው ፣ እሱም ገብቶ ተቀመጠ ፤

፪፣ ወነሥአ ባዖስ ፲ተ ዕደወ እምሊቃናተ ሀገር ወይቤሎሙ ንበሩ ዝየ ወነበሩ ፣

ባዖስም ከሀገር ሽማግሌዎች አሥር ሰዎች አምጥቶ በአደባባይ ተቀመጡ አላቸው ፣ እነሱም ተቀመጡ ፤

፫፣ ወይቤሎ ባዖስ ለመስተሐምው መክፈልተ ገራህት ዘእኁነ አቤሜሌክ አግብእ ላቲ ለኑሐሚን እንተ አተወት እምሐቅለ ሞዓብ ፣

ባዖስ መውረስ የሚገባውን ሰው የወንድማችን የአቤሜሌክን ዕጣ ከሞዓብ አውራጃ ለተመለሰች ለኑሐሚን መልስላት አለው ፤

፬፣ ወአንሰ ነገርኩከ ትስማዕ እንዘ እብል ኅረይ ለከ በቅድመ እለ ይነብሩ ወበቅድመ ሕዝብ እመሰ ትትሐመው ተሐመው ወእመሰ ኢትትሐመው አይድአኒ ፣

እኔ ትሰማኝ ዘንድ በአደባባይ በተቀመጡ በአለቆችና በሕዝቡ ፊት የሚሻልህን ምረጥ ብዬ ነገርኩህ አወራረስ የሚገባ ለእኔ ነው ትለኝ እንደሆነ ውረስ ፣ አልወርስም ትለኝ እንደሆነም ንገረኝ ፤

ወአእምር እስመ ዘይቀድምስ ተሐምዎ አንተ ወአነ እምድኅሬከ ወይቤሎ አነኑ ውእቱ መስተሐምው ፣

አስቀድሞ አወራረስ አቆራረስ የሚገባህ አንተ ነህና ከአንተ ቀጥዬ እኔ ነኝ እና ልውረስ የማትል ከሆነ መርምረህ እወቅ /እኔ ልወቅ/ አለው ፣ እርሱም ወራሹ እኔ ነኝን አለው ፣ አይቻለኝም ድሀ ነኝ ማለቱ ነው ፤



፭፣ ወይቤሎ ባዖስ ከመ ነሣእከ ገራህተ እምእደ ኑሐሚን ወእምነ ሩት ሞአባዊት ብእሲቱ ለዘሞተ ወኪያሃኒ ርቱዕ ትንሣእ ከመ ታቅም ስሞ ለዘሞተ ላዕለ ርስቱ፣

ባዖስም ከኑሐሚን እጅና ከሚቱ ከመሐሎን ሚስት ከሩት እጅ ርስቱን እንደወሰድኸ አሁንም እሷን አግብተህ በርስቱ ላይ የሞተውን ሰው ስሙን ታስጠራለት ዘንድ ይገባል አለው ፤

፮፣ ወይቤ መስተሐምው ኢይክል ተሐምዎ ከመ ኢይኅጉል ርስትየ ተሐሞ ለርእስከ ተሐምዎ ዘዚአየ እስመ ኢይክል ተሐምዎ ፣

ያም መውረስ የሚገባው ሰው ርስቴን እንዳላጣ መውረስ አይቻለኝም አለ ፣ ርስት ከበዛ ይጠፋልና ፤ አንድም ይህን ርስቴን እንዳላጣ ብዬ ላገባት አይቻለኝም ፣ እኔ የሁለት ሴት ቤት መሥራት ሁለት ሴት ማሳደር አይቻለኝምና ለእኔ የሚገባውን አወራረስ አንተ ውረስ አለው ፤

፯፣ ወከመዝ ውእቱ ኵነኔሁ ለተሐምዎ በቅድመ እስራኤል ወበእንተ ተዋልጦ ከመ ያቅም ቃሎ ፣

በእስራኤል ፊት የአወራረስ ሥርዓት እንዲህ ነው ፣ ቃሉንም ያፀና ዘንድ አወራረሱን የሚለውጥ ሰው እንዲህ ነው ፤ አንድም ሚስቱን በአወራረስ የሚለውጥ ሰው ሥርዓቱ እንደዚህ ነው ፤

ወይፈትሕ ውእቱ ብእሲ ሣዕኖ ወይሁቦ ለካልኡ ዘይትሐመው ተሐምዎ ዚአሁ ወከመዝ ውእቱ ስምዑ በውስተ እስራኤል ፣

ያ ሰው ጫማውን አውልቆ አወራረስ አቆራረስ ለሚገባው ለወንድሙ ይሰጠዋል ፣ በእስራኤልም ዘንድ ምስክሩ /ምስክርነቱ/ እንዲህ ነው ፤ ሐተታ ጫማ ለእግር ጽንዕ ወይም ቤዛ እንደሆነ ጽንዕ የሚሆን ልጅ ለወንድሜ እወልድለት ነበረ ፣ ቀረብኝ አንተ ግን አግብተህ ውለድለት ሲል ፤ አንድም እኔ ሥርዓት አፍራሽ ነኝ ፣ አንተ ግን በሥርዓት አለህ ሲል ነው ፣ በዚህም ቤተ ፍቱሐነ አሣዕን እየተባሉ ሲሰደቡበት ኑረዋል ፤

፰፣ ወይቤሎ መስተሐምው ለባዖስ ንሣእ ለከ ተሐምዎ ዘዚአየ ወፈትሐ ሣዕኖ ወወሀቦ ፣

አወራረስ የሚገባው ሰውም ባዖስን ለእኔ የሚገባኝን አወራረስ አንተ ውረሰው ብሎ ጫማውን አውልቆ ሰጠው ፤

፱፣ ወይቤሎሙ ባዖስ ለሊቃናት ወለኵሉ ሕዝብ ስምዑ አንትሙ

www.ethiopianorthodox.org

ዮም ከመ ነሣእኩ ኵሎ ዘአቤሜ
ሌክ ወኵሎ ንዋዮሙ ለኬሌዎን
ወለመሐሎን እምእዴሃ ለኑሐ
ሚን ፤

ባዮስም አለቆቹንና ሕዝቡን
የአቤሜሌክን ገንዘብ የኬሌዎ
ንንና የመሐሎንንም ገንዘብ
ሁሉ በአወራረስ ከኑሐሚን
እጅ ዛሬ እንደተቀበልሁ
ስሙ ፤

፲፤ ወለሩት ሞዓባዊት ብእሲተ
መሐሎን ነሣእክዋ ሊተ ትኩነኒ
ብእሲተ ወከመ አቅም ስሞ ለዘሞተ
ላዕለ ርስቱ ወኢይጥፋእ ስሙ
እምአኃዊሁ ወእምነገደ ሕዝቡ
ስምዕየ አንትሙ ዮም ፤

የሞዓብ ሴት የምትሆን
የመሐሎን ሚስት ሩትንም
ሚስት ትሆነኝ ዘንድ ለሞተው
ለመሐሎን በርስቱ ላይ ስሙን
የሚያስጠራ ልጅ እወልድለት
ዘንድ ከወገኑ ነገድና ከወንድ
ሞቹ ተለይቶ ስሙ እንዳይ
ጠፋ እንዳገባኋት ዛሬ እናንተ
ምስክሮች ናችሁ አላቸው ፤

፲፩፤ ወይቤሉ ኵሉ ሕዝብ በኆበ
አንቀጽ ስምዕከ ንሕነ ፤

በአደባባይ የተቀመጡት
ሕዝቡ ሁሉም እኛ ምስክሮ
ችህ ነን አሉ ፤

ወሊቃናትኒ ይቤልዎ ይረስዮ ለከ
እግዚአብሔር ለብእሲትከ እንተ
ትበውእ ውስተ ቤትከ ከመ
ራሄል ወከመ ልያ እለ ሐነጸሁ
ለቤተ ፳ኤል ፪ኤሆን ወግበር
ኃይለ ውስተ ኤፍራታ ወይኩንከ
ስም በውስተ ቤተ ልሔም ፤

ሽማግሌዎችም ወደቤትህ
የምትገባ ይህችን ሚስትህን
እግዚአብሔር ለአንተ የያዕ
ቆብን ቤት እንደ አነጹት
/እንደ አጸኑ/ እንደ ሁለቱ
እንደ ራሔልና እንደልያ ያድ
ርግልህ፤ በኤፍራታም ኃይልን
አድርግ በቤተልሔምም ስም
የሚያስጠራ ልጅ ይስጥህ
አሉት ፤

፲፪፤ ወይኩን ቤትከ ከመ ቤተ
ፋሬስ ዘወለደት ትእማር ለይሁዳ
ወዘርአ የሀብከ እግዚአብሔር
በላዕለ ዛቲ ወለት ፤

ወገንህም ትእማር ለይሁዳ
እንደወለደችለት እንደ ፋሬስ
ወገን ይሁን እግዚአብሔርም
ከዚህች ልጅ ዘር ይስጥህ
አሉት ፤ አንድም እግዚአብ
ሔር ትእማር ለይሁዳ
የወለደችለት የፋሬስን ቤት
እንደ አጸና የአንተንም ቤት
በልጅ በከብት ይነጽልህ
/ያጽናልህ/ አሉት ፤

፲፫፤ ወነሥአ ባዮስ ለሩት ወኮነቶ
ብእሲተ ወወሀባ እግዚአብሔር
ወፀንሠት ወወለደት ወልደ ፤

ባዮስም ሩትን አገባት ፤ ሚስት
ሆነችው፤ እግዚአብሔርም



ልጅ እንድትወልድ አደረገ ፤
ፀንሳም ወንድ ልጅ ወለደች ፤

፲፬፤ ወይቤላሃ አንስት ለኑሐሚን
ይትባረክ እግዚአብሔር ዘኢያኅጥ
አኪ ዮም መስተሐምወ በዘይሰ
መይ ስምኪ በውስተ እስራኤል ፤

ሴቶችም ኑሐሚንን በእስራ
ኤል ዘንድ ስምሽ በሚጠራ
ገንዘብ ዛሬ አወራረስ አቆራ
ረስ የሚገባው ሰው ያላሳጣሽ
እግዚአብሔር ይክበር ይመስ
ገን አሏት ፤

፲፭፤ ወይከውነኪ በዘታገብኢ ነፍ
ስኪ ወዘየሐፅኖ ለሲበትኪ እስመ
አፍቀረተኪ መርዓትኪ እንተ
ወለደት ዘይኄይሰኪ ለኪ እም፯ቱ
ደቂቅ ፤

ልቡናሽን ከኀዘን ወደ ደስታ
በምትመልሽ ገንዘብ የምት
መልሽበት ይሆንሻል ፤ ከሰባት
ልጆች የሚበልጥ ልጅ የወለ
ደችልሽ ምርዓትሽ ወዳሻለ
ችና የአረጀ ሰውነትሽንም
የሚያድሰው ይሆንሻል አሏት፤

፲፮፤ ወነሥአቶ ኑሐሚን ለውእቱ
ሕፃን ወአንበረቶ ውስተ ሕፅና
ወኮነቶ ሐፃኒተ ፤

ኑሐሚንም ያነን ሕፃን ተቀብላ
በክንዷ ታቀፈችው ፤ ሞግዚ
ትም ሆነችው ፤

፲፯፤ ወሰመያሁ አግዋሪሃ ስሞ እንዘ
ይብላ እስመ ተወልደ ወልድ
ለኑሐሚን ወሰመዩ ስሞ ኢዮቤድ
ወውእቱ አቡሁ ለዕሤይ አበ
ዳዊት፤

ጐረቤቶቿም ለኑሐሚን ልጅ
ስለተወለደላት ኀዘንን የሚአ
ስረሳ ሲሉ «ሰመያ ስሞ»
ስሙን ኢዮቤድ አሉት፤
ኢዮቤድም ማለት መርስኤ
ኀዘን መጽንኤ ርስት ፤ ፀዋሬ
ርስአን ማለት ነው፤ ይኸም
ኢዮቤድ የዳዊት አያት የዕሤይ
አባት ነው ፤

፲፰፤ ወከመዝ ውእቱ ትውልዱ
ለፋሬስ ፋሬስ ወለዶ ለኤስሮም፤

«ወይኩን ቤትከ ከመ ቤተ
ፋሬስ ዘወለደት ትእማር
ለይሁዳ» ብሎ ነበርና ከዚያ
አያይዞ ትውልድ ለመቍጠር
አመጣ ፤ የፋሬስ ትውልዱ
እንዲህ ነው ፤ ፋሬስ ኤስሮ
ምን ወለደው ፤

፲፱፤ ወኤስሮም ወለዶ ለአራም
ወአራም ወለዶ ለአሚናዳብ ፤

ኤስሮም አራምን ወለደው ፤
አራምም አሚናዳብን
ወለደው ፤

፳፤ ወአሚናዳብ ወለዶ ለነአሶን
ወነአሶን ወለዶ ለሰልሞን ፤

አሚናዳብ ነአሶንን ወለደው
ነአሶንም ሰልሞንን ወለደው ፤

፳፩፤ ወሰልሞን ወለዶ ለባዮስ ወባዮስ
ወለዶ ለኢዮቤድ ፤

www.ethiopianorthodox.org

ሰልሞን ባዖስን /ቡኤዝን/ ወለደው ፣ ባዖስም ኢዮቤድን ወለደው ፤

፳፪፣ ወኢዮቤድ ወለዶ ለዕሤይ ወዕሤይ ወለዶ ለዳዊት ፣

ኢዮቤድ ዕሤይን ወለደው ፣ ዕሤይም ዳዊትን ወለደው ፤

ተፈጸመ ኦሪት ዘሩት

የሩትን ዜና የሚናገር መጽሐፍ ደረሰ ተፈጸመ ፤

ወስብሐት ለእግዚአብሔር አነሣሥቶ ላስጀመረን አስጀምሮ ላስፈጸመን ለእግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባው::

www.ethiopianorthodox.org